# ስለ ትርጉም ጠቃሚ መርጃ

በሰለጠነ  አስተርጓሚ  እና ባልሰለጠነ አስተርጓሚ ለምሳሌ ጓደኛ ወይንም የቤተሰብ አባል መካከል ያለዉ ልዩነት ምንድን ነዉ?

| |
|---|
| የሰለጠነ አስተርጓሚ ማንኛዉንም ጉዳይ በሚስጥር ይይዛል። እርስዎ ባደርጉዋቸዉ ስብሰባዎች ላይ ስለተወሱት ነገሮች ለማንም አይገልጽም- ለእርስዎ እንደተርጎመም በፍጹም አያሳዉቅም። |

ሌሎች ተጨማሪ ልዮነቶችም አሉ፡

| የሰለጠነ አስተርጓሚ | ያልሰለጠነ አስተርጓሚ |
|---|---|
| • ሚስጢርን ለመጠበቅ በስነምግባር መመሪያ የተገደበ ነዉ | • በስነምግባር መመሪያ ያልተገደበ ነዉ፣ ይህም ማለት የግል ሚስጢርዎትን ለሌላ ሰዉ አሳልፎ ሊሰጥ ይችላል |
| • የተባለዉን ነገር በሙሉ እና በትክክል ያስተላልፋል፣ ፍሬ ነገሮችን ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ ያስተላልፋል | • ፍሬ ነገሩን እና ዝርዝር ሁኔታዉን በትክክል ለማስተላለፉ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፣ በተናገሩት ነገር ላይ ከፍተኛ የትረጉም ለዉጥ ሊያደርስ ይችላል |
| • የንግግር ዘይቤን እና እያንዳንዱን ጥቃቅን የሁኔታ መግለጫ ፣ የነገሮችን ስሜት መግለጫ ለምሳሌ ተአቅቦን፣ ጥርጣሬን ፣ ተቃዉሞን፣ መስማማትን እንዳሉ ያስተላልፋል | • ነገሮችን ያለዝባል ወይንም ለማሳመር የሚረዱ ለዉጦችን ያደርጋል፣ በጣም ጠቃሚ የሆኑ መርጃዎችንም ያስወግዳል |
| • ካልተረዳዎት ይህንኑ ይገልጽልዎታል እናም ተጨማሪ ማብራሪያ ይጠይቃል | • ያልተረዳዉ ወይንም በጣም የተወሳሰበ ወይንም ቴክኒካል የሆነ መረጃ ከሆነ ዝምብሎ በመቀባጠር ሊያልፈዉ ወይንም ሊተወዉ ይችላል |
| • ትክክኛነትን ለማረጋገጥ ማስታዎሻ ይይዛል | • በተለየ ስልጠና ካልታገዘ በስተቀር በአጠቃላይ ትክክለኛ ባልሆነዉ በአጭር ጊዜ የማስታወስ ብቃቱ ይተማመናል |
| • ማብራሪያ ለመጠየቅ ሊያስቆምዎት ወይንም ትክክኛነቱን ለማረጋገጥ ሊያስደግምዎት  ይችላል | • ማብራሪያ ለማግኘት ወይንም መርጃዉን ለማጣራት ስለማያስቆምዎት አንደበተ ርቱዕ ይመስላል |
| • ማድርግ ስለሚገባዉ ገደብ ያዉቃል በማንኛዉም ጊዜ ገለልተኛ ነዉ። ከማስተርጎም ዉጭ ምን አይነት ተግባር አያከናዉንም፣ የግል አስተያየቱን ወይንም ምክር አይሰጥም። | • ማድርግ ስለሚገባዉ ገደብ አያዉቅም፣ የግል አስተያየቱን ወይንም ምክር ይሰጣል፣ ወይንም ሌሎች ተግባሮችን ያከናዉናል ለምሳሌ ያህል የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጣል። |
| • ስለሚያስተርጉምበት አካባቢ በቂ ስልጠና ወስዷል | • ምንም አይነት ስልጠና አልወሰደም |

## ያልሰለጠነ  አስተርጓሚ  ወይንም  የቤተሰብ  አባልን  እንደ  አስተርጓሚ  በመጠቀም እራስዎን እና ቤተሰብዎን ለችግር አይዳርጉ

## መብቶችዎ ምንድን ናቸዉ?

ለብዙ ጉዳዮች አስተርጓሚ እንዲኖርዎት መጠየቅ መብትዎ ነዉ።

- ከመንግስት ባለስልጣን፣ ከሆስፒታሎች፣ ከፍርድ ቤት ወይንም ከፖሊስ ጋር ጉዳይ ሲኖርዎት የሰለጠነ (ፕሮፌሽናል) አስተርጓሚ የማግኘት መብት አለዎት። በዚሁም መሰርት  የሰለጠነ አስተርጓሚ ለመጠየቅ አይሸማቀቁ ወይንም አይፈሩ።
- የአስተርጓሚዉን ሁኔታ መምርጥ ይችላሉ፣ አስተጓሚዉ ፊት ለፊት ተገኝቶ ወይንም የስልክ አስተጓሚ እንዲሆንልዎት። ለረጅም ወይንም ለተወሳሰበ ምክክር ወይንም ስሜታዊ ለሆኑ ጉዳዮች የስልክ አስተጓሚ አይመከርም።
- ምንም እንኳን የእርስዎ የእንግሊዘኛ ችሎታ ጥሩ ቢሆንም ሰዎች እራሳቸዉን በተገቢዉ እና በጥሩ ሁኔታ መግለጽ የሚችሉት በራሳቸዉ ቋንቋ በመሆኑ የራስዎትን ቋንቋ የመጠቀም መብት አለዎት። በብዙ ሁኔታዎች እንግሊዘኛን በሙሉ ልብ ለመጠቀም ሊያቅትዎ ይችል ይሆናል፣ ወይንም የህክምና ወይንም የህግ ቃላቶችን ላያዉቁዋቸዉ ይችላሉ፣ ወይንም የባለሙያዉን የንግግር ቅላጼ (ዘይቤ) ላይረዱት ይችሉ።

## አስተርጓሚ እንዴት ማግኘት ይችላሉ?

- እንግሊዘኛ ከሚናገር ባለሙያ ጋር ቀጠሮ ሲኖርዎት በቅድሚያ የሰለጠነ አስተርጓሚ እንዲኖር ይጠይቁ። ኤጀንሲዉ አስተርጓሚ እንዲኖርዎት የማመቻቸት ግዴታ አለበት፣ በአብዛኛዉ ጊዜም የአስተርጓሚዉን ክፍያ መሸፈን ይጠበቅበታል።

## መጥፎ የሆነ አስተርጓሚ ከገጠመዎት ምን ማድርግ ይችላሉ?

- እባክዎትን ቅሬታዎትን ያሰሙ። እርሰዎ ቅሬታዎትን ካላሰሙ ምንም ነገር ሊለወጥ አይችልም ሌሎች የእርስዎ ማህበርሰብ አባላትም ተመሳሳይ ችግር ይገጥማቸዋል በተጨማሪም ማንም ላያሰተዉለዉ ይችላል። ለዉጡን ካመጡ ግን ማንኛዉም የእርስዎ እና የሌሎች ማህበርሰብ አባላት ተጠቃሚ ይሆናሉ።
- ስለ ጤንነት ሁኔታ ባስተርጎመልዎት ሰዉ ካልተደሰቱ ቅሬታዎትን ለጤናና የአካል ጉዳተኞች ኮሚሽነር ማቅርብ ይችላሉ። የእነሱን ቅሬታ ማቅርብ እና ማስወገድ በሚል ርእስ የተተረጎመዉን በራሪ ጹሁፍ ማግኘት ይችላሉ ወይንም ስለ መብትዎ በርስዎ ቋንቋ ከድረ ገጻቸዉ:  http://www.hdc.org.nz/complaints ያዳምጡ።

## እባክዎትን ይህንን ጽሁፍ ለማህበርሰቡ አባላት በሙሉ ያስተላልፉ።

አስተርጓሚ ለመጠየቅ ይህንን ገጽ ይዘዉ ይሂዱ፡

| | |
|---|---|
| I speak Amharic<br><br>I need an interpreter, preferably<br><br>☐ Onsite<br><br>☐ Telephone | የምናገረዉ ቋንቋ አማርኛ<br><br>አስተርጓሚ እፈልጋለሁ፣ ቢቻል<br><br>☐ በቦታዉ<br><br>☐ በስልክ |

ለተጨማሪ መረጃ:

ስልክ: (04) 384 2849 ወይንም 0508 468 3777

ኢሜይል: info@interpret.org.nz

የኒዉ ዚላንድ ትርጉምን ድረ ገጽ ይጎብኙ: www.interpret.org.nz